# የይሁዳ መልዕክት (19)

## ጥናት አንድ (ይሁዳ ቁጥር 1-7)

የጥናት ዓላማ:- እግዚአብሄር እኛ ልንወስደው ከቀድነው እቅድ ውጭ የተለየ ሃሳብ እንዳለው ሙሉ ልባችን ከተቀበለው ፕላናችንን ለመቀየር የተዘጋጀን ልንሆን እንደሚገባን ለመማር::
የምናሰላስለው ጥቅስ: «ወዳጆች ሆይ አብረን ስለምንከፈለው ድነት ልጽፍላችሁ እጅግ ጓጉቼ ነበር፤ ነገር ግን ለቅዱሳን አንዴና ለመጨረሻ... እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ:: ይሁዳ 3

1. የይሁዳ መልዕክት 1:1-16 በአንድነት ይነበብ:: ቁ1 ስለ ጸሐፊው ስለራሱ የሚነግረን ነገሮች ምን ምንድናቸው? ከእነዚህ ልንማር የምንችላቸው ምን ነገሮች ይኖራሉ?
2. እዚሁ ቁ1 ላይ በማናቸውም እውነተኛ ክርስትያን ህይወት እውነት የሆኑ ሶስት ሃሳቦችን ይጠቅሳል:: እነዚህ ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
3. ይሁዳ ይህንን መልዕክት ከመጻፉ በፊት ሊጽፍ ያሰበው ስለምን ሊጽፍ ነበረ? ስለ ደህንነት ከመጻፍ ስለ ሃሰተኛ አስተማሪዎች መጻፍ ስለሚሻል ነው ወይስ ለምን ሃሳቡን የቀየረ ይመስልሃል?
4. ጸሐፊው ደህንነታችንን በተመለከተ እንዳሰበው ቢጽፍ ከሚያከትታቸው ሃሳቦች ውስጥ መኖሩ አይቀሬ ነው የምትለውን ሃሳብ ተናገር:: «ይሁዳ» የስሙ ትርጉም ምንድነው?
5. ቁ4 ስለነዚህ ሃሰተኛ አስተማሪዎች የሚገልጣቸውን አምስት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር::
6. «ይህንን ሁሉ የምታውቁ ቢሆንም... ላስታውሳችሁ እወዳለሁ::» ቁ5 ለምንድነው የሚያውቁትን ነገር ማስታወስ ያስፈለገው?
7. በቁ5-7 ላይ የሃሰት አስተማሪዎቹን በብሉይ ኪዳን ከሆኑ ከሶስት ሁኔታውች ጋራ ያመሳስላቸዋል:: እነዚህ ሁኔታዎች ምን ምንድናቸው? ለሁኔታዎች የጋራ የሆነው ሃሳብ ምንድነው? ታዲያ ሊናገር ለሚፈልገው ሊሰጠን የፈለገው ትምህርት ምንድነው?
8. የመጀመሪያውን ሃሳብ ቢከተልና ይህንን መልዕክት ባይጽፍ የሚጎድልብህ ነገር ይኖር እንደነበረ ታምናለህ ወይ? አዎን የምትል ከሆነ ምን ይጎልብህ እንደነበር ዘርዝረህ ተናገር:: ከራስህ ዕቅድ ይልቅ የመንፈስ ቅዱስን ማስቀደም ምን ያህል ተለማምደሃል?

# ጥናት ሁለት (ይሁዳ ቁጥር 8-16)

የጥናት ዓላማ:- በቁ16 ላይ የተዘረዘሩት ሃጥያቶች እውነተኛ አማኞችንም የሚያስቸግሩ ነገሮች እንደሆኑ በማስገንዘብ በተለይ ግን ለጥቅም ሲባል ሰዎችን ማሞጋገስና መከብ በእግዚአብሄር ዘንድ አጸያፊ ነገር እንደሆነ በዚህ ትምህርት ትኩረት በመስጠት ለማስገንዘብ፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ: «...ጥቅም ለማግኘት ሲሉ ሌሎችን ይክባሉ፡፡» ይሁዳ ቁ16

1. ይሁዳ ቁ8-16 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁጥር 8 ሲጀምር «እነዚህ ህልም አላሚዎች» ይላል ከዚህ አባባሉ ስለነዚህ ሰዎች ሊናገር የፈለገው ነገር ምን ይመስልሃል?
2. ሃሰተኛ አስተማሪዎቹ የሚያደርጓቸው ሶስት ነገሮች ቁ 8 ላይ ተዘርዝረዋል፡፡ እነዚህ የተዘረዘሩት ነገሮች ምን ምንድናቸው? በተለይ በዚሁ ክፍል «የመላዕክት አለቃ የሆነው ሚከኤል እንክዋ...» በማለት ሊያስጠነቅቀን የፈለገው ነገር ምንድነው?
3. መልዕክቱ ያዘለውን ነገር በመመልከት የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች የተጻፈው ለአይሁድ ክርስትያኖች እነደደሆነ ይናገራሉ፡፡ ይህንን ሊያሰኛቸው የቻለው ነገር ምን ይመስልሃል?
4. በቁ11 ወዮላቸው ያለበት ምክንያቶች ምንድናቸው? እነዚህ እያንዳንዳቸው ምን ማለት እንደሆኑ አስረዳ፡፡
5. በቁ12-14 እነዚህን ሰዎች ይሁዳ የሚመስልባቸውን ነገሮች ዘርዝር፡፡
6. «...ድቅድቅ ጨለማ ለዘላለም የሚጠብቃቸው ተንከራታች ከዋክብት ናቸው፡፡» ይሁዳ የነዚህን ሰዎች የዘላለም ዕጣ ለምን በድፍረት ሊናገር ቻለ ብለህ ታምናለህ? እኛስ እንደዚህ በድፍረት መናገር እንችላለን ወይ?
7. ቁጥር 16 ስለነዚህ ሰዎች ማንነት ያሰፈራቸውን ነገሮች ዘርዝር፡፡ እነዚህ ሁሉ የሚነግሩን ምን እንደሚያስተምሩ ሳይሆን አኗኗራቸውን ነው፡፡ ታዲያ ከዚህ ምን እንማራለን?
8. በዘመናችን በምታየው ክርስትና ከእነዚህ ውስጥ ጎላ ብሎና በብዛት የምታየው የትኛውን ስህተት ነው? በተለይ ለጥቅም ሲባል ሰዎችን መከብ የሚለው እንዴት እንደሚሰራ አስረዳ፡፡ ከዚህ ስህተት አንፃር የራስህን ህይወት መርምር፡፡

# ጥናት ሶስት (ይሁዳ ቁጥር 17-25)

የጥናት ዓላማ፦ ይህ በነጻ የተገኘው የዘላለም ህይወት ከፍጻሜ የሚደርሰው በሰው ጉልበትና ችሎታ ሳይሆን መለኮታዊ ሃይል እንደሚያስፈልገውና ኢየሱስ ለፍጻሜ ሊያበቃን በዚህ ክፍል ቃል እንደገባልን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡«እንዳትወድቁ ሊጠብቃችሁና ያለ ነቀፋና በደስታ በክብሩ ፊት ሊያቀርባችሁ ለሚችለው…» ይሁዳ ቁ 24

1. ይሁዳ 17-25 በአንድነት ይነበብ፡፡ የጌታ ሐዋርያት ስለነዚህ አይነት ሰዎች እንደተነበዩ ቁ17 ይነግረናል፡፡ የትኛው ሐዋርያና በየት ስፍራ ነው ይህንን በመጠቆም የተነገረው?
2. ሐዋርያቱ ስለነዚህ ሰዎች ተናገሩት የሚለው ዋና ሐሳብ ምንድነው? «ርኩስ ምኞታቸውን የሚከተሉ» ማለት ምን ማለት ነው?
3. በቁጥር 19ላይ እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች ስለ መለያቸው የሚናገራቸው ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
4. እነዚህ በቁ20 ላይ እናንተ ግን ስለሚላቸው ሰዎች በዚሁ በይሁዳ መልዕክት የታየህና የተረዳኸውን ተናገር፡፡
5. ለእነዚህ እውነተኛ አማኞች በቁ20-21 ራሳቸውን በተመለከተ የሚመክራቸው ምክር ምን እንደሆነ በመዘርዘር ተናገር፡፡ በእግዚአብሄር ፍቅር ራስን መጠበቅ ምን ማለት ነው?
6. ቁ22-23 የሚያሳየን ሶስት አይነት ሰዎች እነማን ናቸው? ከእያንዳንዱ አይነት ሰው ጋራ ማድረግ ስለሚገባን ነገርስ ምን ይነግረናል?
7. እግዚአብሄር አምላክ በአማኝ ህይወት የሚሰራቸው በቁ24 ላይ የተጠቀሱትን ነገሮች ተናገር፡፡ ቁ24 «እንዳትወድቁ ሊጠብቃችሁ» ቁ1 «በኢየሱስ ክርስቶስ ለተጠበቁት» ከነዚህ አባባሎች ምን የምትረዳው ነገር አለ?
8. የያዝከው የዘላለም ህይወት ከግብ ለማድረስ የማን ድርሻ ነው ብለህ ታምናለህ? ለምን? ደህንነትህ በእግዚአብሄር የሚጠበቅ መሆኑ ምን ያህል ደስታ ይሰጥሃል?